# ለሁሉም ጊዜ አለው

ከትቢያ ተነስተው ፣ ሰማይ ላይ የወጡ
በወንጀል በዝርፊያ ፣ አብጠው የቀበጡ
በግፍ በጭካኔ ፣ ህዝብን የረገጡ
ዛር ሳይሞትባቸው ፣ ሳይገለበጡ
ከላይ ተከስክሰው ፣ ከምድር ሳይፈርጡ
እንደ ወንጀላቸው ፣ በፍርድ ሳይቀጡ
አይኖረኋት ፣ ዝንተ ዓለም ፣ እንዲ እንዳለገጡ
እናት ሆድ ፣ አይገቧት ፣ የትም አያመልጡ ።

አምባገነን ሁሌም ፣ ቁርስ ፣ ምሳ እራቱ
ሀፍረትና ቅሌት ፣ ውርደት ነው ፣ ጥማቱ
ደነዝ በመሆኑ ፣ ቅል እራስ ፣ ፍጥረቱ
ጡንቻው ፣ አንጎል ሆኖ ፣ አፍኖት ትዕቢቱ
ለሱ ፣ ክብሩ ኒሻን ፣ ጌጡና ኩራቱ
አይበቃው መጠላት ፣ በህዝብ መተፋቱ
ተረግጦ ካልሆነ ፣ ካልመጣ ቅሌቱ
እንደ ውሻ ፣ አሟሟት ፣ ካልሆነለት ሞቱ
የልቡም አይሞላ ፣ ጠብ አይል ፣ አንጀቱ ።

የሂትለር ፣ የስታሊን ፣ አምሳያ አረመኔ
አገሬን ህዝቧንም ፣ ገዳይ በጭካኔ
የንግዴ ልጅ ፣ ሁሉ ፣ አጋዚ ወያኔ
ቀን ጎድሎ ፣ በናንተም ፣ ያሳየኛል አይኔ
እናንተም ስትሉ ፣ በተራችሁ ወይኔ ።

ተፈርቶ የኖረ ፣ አንዳች ያልበገረው
በሃያልነቱ ፣ በሩ ያልተደፈረው
ማን አለ ፣ ያልወደቀ ፣ ገናና የነበረው ?
ከሞት ፣ አፋፍ ቆሞ ፣ ሁሌ የሚፎከረው
አፈጣጠር ሆኖ ፣ ታሪክ አያስተምረው
የነቃው ወያኔም ፣ የተሰባበረው
ጽዋውን ይጠጣ ፣ ይጋት ከሚመረው
ለሁሉም ፣ ጊዜ አለው ፣ ደርሷል የማይቀረው ።

ታዛቢው … November 18/2011

EthioLion.Com